# የመንፈስ ዝለት መንሥዔና መፍትሔ

*በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሣዊ የግብፅ*
*ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ*

*ውርስ-ትርጉም*
*በዲያቆን ወንድወሰን ሶርሳ*

## ማውጫ


- መግቢያ.......... I
- የመንፈስ ዝለት .......... 1
- የመንፈስ ዝለት ዓይነቶች .......... 2
- የመንፈስ ዝለት ምልክቶች.......... 3
  - ➢ ከፍቅር ጉዞ ወደ ከንቱ መመላለስ.......... 3
- የመንፈስ ዝለት መንሥኤና መፍትሔ .......... 5
  - ➢ ለመንፈሳዊ ሕይወት የምናውለው ጊዜ ማጣት......5
  - ➢ ከንስሐ ርቆ መገኘት.......... 8
  - ➢ በጥቂት ነገር መርካት.......... 9
  - ➢ በመንፈሳዊ ሕይወት የኃላፊነት ቦታዎች አደጋ ......10
  - ➢ ለሌሎች ብሎ መሥራት .......... 14
  - ➢ መንፈሳዊ ተግባራትንና የጸሎት ሰዓታትን መዘንጋት...15
  - ➢ መንፈሳዊ ሕይወትን እንደተራ ነገር አድርጎ መገመት...16
  - ➢ በሕይወት ውስጥ ያለ ከንቱ ምኞት .......... 16
  - ➢ ትዕቢት.......... 19
  - ➢ የትሕትናን ጊዜ አሳጥሮ ለመደሰት መቸኮል.......20
  - ➢ ቸልተኝነትና ለኃጢአት ቦታ መስጠት.......... 20


## መግቢያ

የመንፈስ ዝለት ማለት አንድ ሰው አስቀድሞ የነበረው መንፈሳዊ ሕይወት ማሽቆልቆል፣ዝቅ ማለት ወይም መድከም ነው:: ድካሙም ከቅዱሳን ጀምሮ በክርስትና ሕይወት የሚመላለስ ማንኛውንም ሰው ያጠቃል:: ፈተናውም እንደሰው መንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ የሚለያይ ሲሆን ከራሱ ከመንፈሳዊው ሰው፣ ከዲያብሎስ፣ ከዓለም ፈተና፣ ከክፉ ባልንጀርነት ወይም ይህ ሰው አዘውትሮ ከሚውልበት ቦታ፣ ከሚያነባቸው፣ ከሚሰማቸውና ከሚመለከታቸው ነገሮች ተጽእኖ ሊፈጠር ይችላል::

ቤተክርስቲያናችን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ተወልደው ከሥላሴ የፀጋ ልጅነትን ያገኙ ብዙ ልጆች አሏት:: እነዚህም ልጆቿ በከፍተኛ መንፈሳዊ ቅናትና ትጋት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይመላለሳሉ:: *ነገር ግን «የእነዚህን ምእመናን ሕይወት እንዴት ጠብቆ እስከመጨረሻ እንዲፀኑ ማድረግ ይቻላል?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ሊሆን የሚችለው በመንፈሳዊ ሕይወት ትጋታቸው እንዲቆዩ ከመንፈስ ዝለት ራሳቸውን በመጠበቅ የበለጠ በእምነት እንዲፀኑ በማድረግ ብቻ ነው::*

ስለዚህም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሣዊ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ "የመንፈስ ዝለት መንሥኤና መፍትሔ (Spiritual Languor)" በሚል ርዕስ የጻፉት መጽሐፍ እጅግ ጠቃሚ ሆኖ በማግኘቴ ለመተርጎም ተነሣሥቻለሁ:: በመጽሐፉ ውስጥ ስለመንፈስ ዝለት ምንነት፣ ዓይነቶች፣ መንሥኤና መፍትሔ እንዲሁም በጸሎትና በቤተክርስቲያን የአገልግሎት ሕይወት ውስጥ እንዴት እንቅፋት እንደሚፈጥር በስፋትና በጥልቀት ተብራርቷል::

ተርጓሚው

## የመንፈስ ዝለት

የመንፈስ ዝለት ማለት የነበረን መንፈሳዊ ስሜት፣ ፍላጎት መቀነስ ወይም እያነሰ መሄድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በመንፈስ የምንቃጠል እንድንሆን «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ» /ሮሜ. 12÷11/ በማለት ይመክረናል።

- በበዓለ ጴንጤቆስጤ መንፈስ ቅዱስ በእሳት ላንቃ አምሳል መውረዱ ተጽፏል። /የሐዋ. 2÷3/
- እግዚአብሔር በሲና ተራራ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ የተገለጠለት በቁጥቋጦ ላይ በሚነድ እሳት አምሳል ነው። /ዘፀአ.3÷2/
- እንዲሁም በሌላ ሥፍራ «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነው» /ዕብ. 12÷29/ የሚል ንባብ ይገኛል።

በመሆኑም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው ሁሉ በመንፈስ የሚቃጠል ሊሆን ይገባዋል። ይህም በመንፈስ መቃጠል የሚገለጠው አንድ መንፈሳዊ ሰው በሚያሳየው ፍቅር፣ ጸሎት፣ አምልኮትና አገልግሎት ነው። ፅኑ ክርስቲያን ሕይወቱ በቅዱስ መንፈስ የተቃኘ ነው። የእርሱ መንፈሳዊ ሕይወት ለሌሎች ብርሃን ይሆናል፣ በእርሱ እምነት፣ በርሱ ቅናት ሌሎች ይቃኛሉ።

መንፈሳዊ ሰው እግዚአብሔርንም ሰዎችንም ያፈቅራል።ፍቅሩም የማይለወጥ፣ ብዙ መከራና ፈተና የማያጠፋው ነው። ቅዱስ መጽሐፍም ፍቅርን ከእሳት ጋር ያመሳስለዋል። «ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም» /መኃ. 8÷7/እንዲል።

በፍቅር የተመላ አገልጋይም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈሳዊ ሕይወት በፅኑ ይጋደላል። የአገልጋዩም ሕይወት ለሌሎች ይተርፋል።«...በድካም አብዝቼ÷ በመገረፍ አብዝቼ÷ በመታሰር÷ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሶስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሶስት ጊዜ ተሰበረ ሌሊት ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ።... የቀረውን ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብደኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው።» /2ቆሮ.11÷22-29/

የእግዚአብሔርን ሥራ በመንፈሳዊ ፍቅርና ቅናት ስለሚሠሩ ቅዱሳን መላእክትን ልበ አምላክ ዳዊት እንዲህ ይላል።«መላእክቱንም መንፈስ የሚያደርግ፤ አገልጋዮችንም የእሳት ነበልባል» /መዝ. 103÷4/

ነገር ግን ብዙዎች ምንም እንኳን መንፈሳዊ ነን ቢሉም በተለያዩ ምክንያቶች በመንፈስ እየዛሉ ስለሚሄዱ መንፈሳዊ ትጋትና ቅናታቸውን ይዘው እንዳይቆዩ ያደርጋቸዋል።

ይጸልያሉ ግን በተለመደው ፍቅር ወይም ተመስጦ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉ:: ነገር ግን አይመሩበትም:: መንፈሳዊ ጉባዔያት ወይም ጸሎተ ቅዳሴ ይሳተፋሉ በልቦናቸው ላይ ግን እንደቀደመው የሚያሳድርባቸው ለውጥ የለም:: አምልኮታቸው ነፍስ እንደተለየው ሥጋ ነው:: /2ጢሞ 3÷5/ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር መሆኑን ያውቃሉ:: ሆኖም እግዚአብሔር በጸሎት ጊዜ ከአጠገባቸው እንዳለ አያስተውሉም::

ሐዋርያው ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ እግዚአብሔር ምንኛ በመንፈስ መዛልን እንደሚጠላ ይናገራል:: የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን አለቃ «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ:: በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር:: እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድ ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው::» /ራእ. 3÷15-16/ በማለት ገሥጾታል::

የመንፈስ ዝለት ከሚፈትነው ሰው አንፃር የሚመዘን አንፃራዊ ነገር ነው:: ይህም ማለት ለቅዱሳን ሰዎች ድካም የምንለው ለምእመናን የክርስትናቸውን መሠረት የሚነቀንቅ ሊሆን ይችላል:: ቅዱሳን የመንፈስ ዝለት ካሉበት ከፍተኛ ደረጃቸው ጥቂት ዝቅ ቢያደርጋቸውም ከሌሎች ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት እጅግ ይልቃሉ::

## የመንፈስ ዝለት ዓይነቶች

የመንፈስ ዝለት ዓይነቶች ሦስት ናቸው:: እነርሱም:-

1. _ተራ ዝለት_ ይህ ሁሉንም ሰው ቅዱሳንንም ሳይቀር የሚያጋጥም ነው:: ልዩ ልዩ ምክንያቶችን ተከትሎ የሚመጣና በጠንካራው መንገድ ወደፊት ከመጓዝ እንድናፈነግጥ የሚገፋፋን ነው:: ለምሳሌ:-እናቶች በወሊድ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ሲርቁ፣በሕመም ወቅት መንፈሳዊ ተግባራትን አለመፈጸም እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ::
2. _አንፃራዊ ዝለት_ ይህ አንፃራዊ ሲሆን የሚመጣውም በመንፈሳዊ ሰው ሕይወት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ጊዜያትን ስናነጻጽር ነው:: ለምሳሌ:-በዐቢይ ጾም ወቅት ያለ መንፈሳዊ ትጋት በበዓለ ሃምሳ አይታይም::
3. _አደገኛ ዝለት_ ይህ ዓይነቱ ዝለት ደግሞ በውስጣችን ተቀብሮ ወይም በበግ ለምድ ተሸፍኖ ለራሳችን እንኳን ሳይታወቀን የምንለምደውና ከመልመዳችንም የተነሣ ከርሱ ለመላቀቅ ምንም ጥረት እንዳናደርግ የምንቸገርበት ነው::

ምሳሌ:- ብዙዎች ከመልመዳቸው የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ያለ ፍርሃትና ክብር ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ውስጥም መሆናቸው ምንም



ስሜት ሳይሰጣቸው እናያለን:: እንዲያውም የራሳቸውን ትተው ሥርዓት ለማክበር በሚል ሽፋን ሌሎችን ሲዘልፉ፣ ኃይለ ቃልም ሲናገሩ ይስተዋላል:: አደገኛ ዝለት ያጠቃው ሰው መንፈሱን ቢመረምር ምንም መንፈሳዊ ነገር አያገኝም የሚሠራው ትክክል እንደሆነ በማሰብ ጨርሶውኑ ራሱን አይመረምርም እንጂ::

በመንፈስ ዝለት የተጠቃ ሰው ሳያውቅም ሆነ አውቆ፣ ምክንያት እየሰጠ ከመንፈስ ዝለት አልፎ ወደ ኃጢአት የሚወድቅበት ጊዜ አለ:: ቀስ በቀስም ያለውን ትጎትና በማጣት ለተሾመበት መንፈሳዊ ኃላፊነት ወይንም ለሌሎች ያለውን አክብሮት እያጣ ይሄዳል::

## የመንፈስ ዝለት ምልክቶች

የመንፈስ ዝለት የውድቀት ሂደት ነው:: እንዴት ቢባል ከፍቅር ጉዞ ወደ ከንቱ መመላለስ፣ ከመንፈሳዊነት ወደ ምክንያት ሰጪነት፣ ከመንፈሳዊ ምግባራት ወደ ሥጋ ፈቃድና ከእግዚአብሔር ጋር ከመኖር ይልቅ ከሰዎች ጋር ወደ መጠመድ መውደቅ ነውና::

በሌላ አገላለጽ የጀመርነው መንፈሳዊ ጉዞም የምናንቀላፋበት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትም ጥልቀት የሌለውና በውስጣችን የለበስነው ሳይሆን ውጫዊ ብቻ ይሆናል ማለት ነው::

## ከፍቅር ጉዞ ወደ ከንቱ መመላለስ

መንፈሳዊ ሕይወት እግዚአብሔርን በመውደድ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይህ ፍቅርም የሁሉም ምግባራት መነሻ ነጥብ ሊሆን ይገባል:: የምንጸልየው እግዚአብሔርን ስለምንወደው ነው:: «... ነፍሴ አንተን ተጠማች÷ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች እንጨትና ውኃ በሌለበት ምድረ በዳ» /መዝ. 62÷1/ «አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው» /መዝ. 118÷ 97/የሚለውን የቅዱስ ዳዊትን ቃል እያሰብን ::

የመንፈስ ዝለት ካለ ግን ጸሎት ከፍቅር የመነጨ መሆኑ ቀርቶ ኀሊናችን እንዳይወቅሰን ስንል ብቻ የምንፈጽመው ተግባር ይሆናል:: የእውነተኛ ጸሎት መለኪያ የሆኑት ከፍተኛ ስሜትና መመሰጥን ያጣል:: ትሕትና፣ አክብሮት ወይም ፍቅር የሌለው ይሆናል ሌሎችም መንፈሳዊ ተግባራት ሁሉ እንዲሁ ከመንፈሳዊነት ያፈነግጣሉ::

እንዲህ ባለ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን የምናነበው በማስተዋል፣ በጥልቀት፣ በማሰብ ወይም በሕይወታችን ለመተርጎም አልያም የእግዚአብሔርን ቃል ከመጠማት አንጻር ሳይሆን እንደተለመደ ተግባር አድርገን ነው:: ክቡር ዳዊት ግን ከዚህ ፈጽሞ በተለየ መልኩ «ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ» /መዝ. 118÷162/ በማለት ለቃለ እግዚአብሔር እንዴት ያለ ግምት እንደሚሰጥ ይነግረናል::

ምናልባት መንፈሳዊ ሕይወትን ስንጀምር ለእግዚአብሔር ፍቅር ኖሮን ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን አልገፋንበትም፡፡ ለምን?

- ይህ ድካም የመጣው ምናልባት በጸሎት ጊዜ ከተመስጦ ይልቅ በብዛት ላይ በማተኮራችንና በቀመር በሚመራ ሕይወት ለመመራት በማሰባችን ይሆናል፡፡
- ጸሎት ስናደርስ እኛን የሚያሳስበን ምን ያህል ምዕራፍ እንደደገምን እንጂ እነዚህን በምን ዓይነት መልኩ እንደጨረስን አይደለም፡፡
- በትእዛዝ የተደነገገው የምዕራፎች ቁጥር ላይ ከደረስን በቂዬ ነው ብለን እግዚአብሔር በጸሎታችን፣ በአምልኮታችን ተደስቷል ወይ? የሚለውን ዐቢይ ጥያቄ ግን አናስተውልም፡፡ እዚህ ነጥብ ላይ ስንደርስ ቅዱስ ማር ይስሐቅ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃል፡፡ «በእግዚአብሔር ፊት የቆምሁት ቃላት ለመቁጠር አይደለም፡፡» ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እልፍ ቃላትን በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በማስተዋል መናገርን መርጧል፡፡ /1 ቆሮ. 14÷19/

ብዙዎቻችን ግን ቁጥሩና ብዛቱ ላይ ስለምናተኩር ጸሎታችን በችኮላ ስለሚደረግ ማስተዋል የለበትምና ምንም ዕርባና አይኖረውም፡፡

ስለዚህም ጸሎት መጸለይ ስላለበት ብቻ የሚፈጸም ግዴታ ወደ መሆን ሲለወጥ ከእግዚአብሔር ጋር በፍቅር በመነጋገራችን ደስተኛ ሳንሆን ሕጉን መተግበር ብቻ ዓላማችን ይሆናል፡፡ ከትክክለኛ ዓላማ መውጣታችን ደግሞ ወደ መንፈስ ዝለት ይመራናል፡፡ ጸሎታችንም ምንም ፍሬ ሳይኖርበት ይጠናቀቃል፡፡

ብዙ ክርስቲያኖች መዝሙረ ዳዊትን ይደግማሉ፡፡ በመጀመሪያ ሲማሩ በቃላቸው አጥንተውት ሳይሆን ይችላል፡፡ ሲጸልዩም በዝግታ ሆነው በተመሥጦ ነበር፡፡ ነገር ግን በልምድ /በመደጋገም/ በቃላቸው በያዙት ጊዜ በሚጸልዩበት ወቅት እጅግ ከመፍጥናቸው የተነሣ ከአንደበታቸው ምን እንደወጣ እንኳን አይታወቃቸውም፡፡

ችኮላና ማነብነብ ማስተዋልን ይቀንሳል፡፡ እንዲህም ከሆነ መዝሙራት የጸሎት መንፈስ የተለያቸው ተራ ሙዚቃዎች ይሆናሉ፡፡

ይህ ዓይነት የመንፈስ ዝለት በሚያጠቃን ጊዜ ለራሳችን «እንደ ቀራጩ ጥቂት ነገርም ሆነ በቀኝ እንደተሰቀለው ወንበዴ አንድ ዐረፍተ ነገር ብናገር ጸሎቴ ከእግዚአብሔር ጋር ከልብ እገናኝ ዘንድ ነው፡፡» ልንል ይገባል፡፡

የመንፈስ ዝለት ሌላው ምክንያት ኀሊናን በመሰብሰብ በእርጋታ ከሚጸለይ ጸሎት ይልቅ በማነብነብ መጸለይና ከልብ



የሚመነጩ ሌሎች ቃላትን ሳንጨምር ሸምድደን በያዝነው ጸሎት ብቻ መወሰን ነው፡፡

ነገር ግን መዝሙራትም ሆነ ሌሎች ጸሎታት ምን ያህል ጥልቅ ናቸው? ከልብ ከተረዳናቸው መንፈሳዊ መዛግብት ናቸው፡፡ በነዚህ ጸሎታት ላይ ሌሎች ከልብ የሚመነጩና በራሳችን ቃላት በሚገለጡ በፊቱ እንደቆምን አስበን ለእግዚአብሔር በፍጹም ታዛዥነትና ቅንነት የምናቀርበው ጸሎት ልንጨምርባቸው ይገባል፡፡

በብዛትና ያለፍቅር ሕግን ለመፈጸም ብቻ ከሚል ሕይወት ለመላቀቅ እንሞክር፡፡ በማስተዋልና በጥልቅ ስሜት ሆነን በመንፈስ ለመጸለይ እንትጋ፡፡ ይህንንም በሌሎችም መንፈሳዊ ተግባራት ላይ እንተርጉመው፡፡

የክርስትና ሕይወት ጀማሪዎች ከሆንን አጭር ጸሎት በተመሥጦና በጥልቀት እንጸልይ፡፡ ከዚያም በተመሳሳይ ጥልቀትና ተመስጦ ብዛቱን ለመጨመር እንሞክር፡፡ ካልተቻለ ግን በዚያችው አጭር ጸሎት እንቀጥል፡፡ ምክንያቱም በጣም አስፈላጊውና ከመንፈስ ዝለት የሚያድነን ተመስጦ ነው፡፡

የመንፈስ ዝለት ከጸሎት፣ ከማንበብ፣ ከማሰላሰልና ከሌሎችም መንፈሳዊ ተግባራት አልፎ ወደ ልብ በመዝለቅ ውስጣዊ ስሜታችንን በመንካት በአጠቃላይ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ይጎዳል፡፡ ለአገልግሎት ያለን ፍላጎት ይቀንሳል፣ በቅናትና በቁጭት እናደርገው የነበረውን ተግባርና ራስን መውቀስ በንስሐ ሕይወት ስንመራው የነበረው መንፈሳዊ ሕይወታችን ቀስ በቀስ እየቆረቆዘ ይሄዳል፡፡

## የመንፈስ ዝለት መንሥኤና መፍትሔ

### ለመንፈሳዊ ሕይወት የምናውለው ጊዜ ማጣት

በጣም አደገኛ ከሆኑት የመንፈስ ዝለት ምክንያቶች መካከል አንዱ በሌሎች ነገሮች ተጠምዶ ለእግዚአብሔር (ለመንፈሳዊ ሕይወት) የምናውለው ጊዜ ማጣት ነው፡፡ እንዲህ ባለው ጊዜ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ መስጠት ይቀራል፡፡ በመሆኑም ልቡናን ከሚያነቃቁ መንፈሳዊ ተግባራት ቸል ይባልና የመንፈስ ዝለት ይከተላል፡፡

የምንጠመድባቸው ነገሮች ብዙ ዓይነት ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ዓለማውያን ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በመንፈሳዊ አገልግሎት ይጠቃለላሉ፡፡

አንድ ሰው ምናልባት በቤተሰባዊ ጉዳዮች፣ በአንዳች ሥራ፣በመዝናናት ወይም በትርፍ ጊዜ ሥራ እና በመሳሰሉት በመጠመድ ለመንፈሳዊ ነገሮች የሚያውለው ጊዜ ያጣል፡፡

ይህ ድካም ሳጠቃው ሰው ሁለት ጠቃሚ ሃሳቦችን ማገናት ተገቢ ነው፡፡ እነርሱም፡-

1. ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ወይም ቅድሚያ የሚሰጠውን ማወቅ
2. የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማስታወስ «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» /ማቴ. 16+26/

ጊዜያችንን በአግባቡ ተጠቅመን ለመንፈሳዊ ተግባራት ጊዜ እንሰጥ ዘንድ ደግሞ ከላይ የተገለጸውን የዘላለማዊ ሕይወትን ነገር ማወቅ አለብን። ይህን ወደማወቅ ከመጣን ትኩረታችንን ስለሚስበው ያለንን ጊዜ በማብቃቃት የተወሰነ ጊዜ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን መመደባችን አይቀርም።

በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ በጀመርን ጊዜ ጠንቃቃ መሆን አለብን። ምክንያቱም የመንፈስ ዝለት ሳናውቀው ልቡናችን በማይወቅሰን ሁኔታ ከመንፈሳዊ ተግባራት ሊያግደን ይችላል።

በመንፈሳዊ ሕይወት በደከምን ጊዜ አገልግሎታችንም አብሮ እንደሚላላና ምንም ፍሬ እንደማይሰጥ ማወቅ አለብን። ምክንያቱም አገልግሎት ዝም ብሎ የሚሠራ ሥራ ሳይሆን ከአገልጋዩ ወደ ተገልጋዮች የሚተላለፍ የመንፈስ ፍሬ፣ የሚገለገለው ሰው ከአገልጋዩ የሚቀስመው ሕይወት ነውና።

እግዚአብሔር ከጸሎትና ከእርሱ ጋር የሚኖረንን ምሥጢራዊ ሕይወት የሚለይን አገልግሎት አይፈልገውም። ለዚህ ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ታላቅ ወንድም ጥሩ ምሳሌ ነው። አባቱን ከሚያገለግልበት እርሻ ሲመለስ «... እነሆ ይህን ያህል ዓመት እንደ ባሪያ ተገዝቼልሃለሁ ከትእዛዛትህም ከቶ አልተላለፍሁም ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጠቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም» /ሉቃ. 15÷29/ በማለት ተናገረ።

የጠፋው ልጅ ታላቅ ወንድም አባቱን ለረጅም ጊዜ ቢያገለግልም ሃሳቡ ከአባቱ የማይገናኝና በመንፈስ ደካማ ነበር። ይህም በአነጋገሩ ታወቀ። ስለዚህ አገልግሎቱ በአባቱ ከመደሰት እንደከለከለው እንደ ጠፋው ልጅ ታላቅ ወንድም ልንሆን አይገባም።

አንዳንዴ ለመንፈሳዊ ሕይወት ስንል ከተወሰኑ ሥራዎችና ኃላፊነቶች ራሳችንን ማግለል ይጠበቅብናል። ለምሳሌ ብዙ ከመዝናናት፣ ከብዙ ስብሰባዎች፣ ብዙ ከማውራት እና ከመሳሰሉት መታቀብ አስፈላጊ ነው።

በብዙ ሥራዎች ብንጠመድም እግዚአብሔርን ዘወትር ልናስበው ይገባል። ምንም ዓይነት ተግባር ቢሆን መላ ጊዜያችንንና ልባችንን እንዲወስድ አንፍቀድለት። ለእግዚአብሔር የሚገባው ጊዜ የታለ?



በማለት ሁል ጊዜ ራሳችንን ልንጠይቅ ያስፈልጋል፤ለእግዚአብሔር የሚገባውን ጊዜ መስጠት ይኖርብናል።

በሥራችን ሁሉ መሀል ጊዜአችን በሙሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ጊዜ የእግዚአብሔር ነው። አራት ጠቃሚ ሃሳቦችን አንስተን የእግዚአብሔርን ድርሻ እንመልከት። እነርሱም፦

1. የጌታን ቀን ቅዱስ አድርገህ ትጠብቀው ዘንድ አስብ።
2. የቀዳማያትን ሕግ ከጊዜያችን አንፃር ማስተዋል።

የጌታን ቀን በመጠበቅ ታማኝ ከሆን ሳምንቱን በሙሉ ከዝለት የሚጠብቀን ትጥቅና ስንቅ አዘጋጀን ማለት ነው። የቀዳምያትን ሕግ ተግባራዊ በማድረግና ከሳምንቱ የመጀመሪያውን ቀን ለእግዚአብሔር ከሰጠን የምናገኘው ጸጋ እለታቱን በሙሉ አብሮን በመሆን እንዲያውም ሌላ ጊዜ እንድናመቻች ይገፋፋናል።

3. ትኩረታችንን ሊሰበው የሚገባው ሌላ ነጥብ፦ቀኑን ሙሉ በሥጋዊ ጉዳዮች ስንባክን የምንውል ከሆነ እነዚህ ልቡናችንንና ኅሊናችንን በቁጥጥራቸው ሥር ያውሉታል። ስለሆነም ለጸሎት በቆምን ጊዜ ኅሊናችን የረጋ አይሆንም። ሌሎች ሃሳቦች ይረብሹናልና።

በመሆኑም በሌሎች ተግባራት መጠመድን እንደ መንፈስ ዝለት ምክንያት ስናነሳ ጊዜን መቆጣጠራቸው ብቻ ሳይሆን በልቡና ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖም ጭምር ነው። አደገኛው ይህ ነው።

4. ቤተ ክርስቲያን በሥራችን መሐል ለተወሰነ ጊዜ ልባችንን ወደ ሰማይ አቅንተን እግዚአብሔርን እናስብ ዘንድ ሰባት የጸሎት ሰዓታትን ወስናልናለች።

እነዚህን በየሦስት ሰዓቱ የሚደረጉ ጸሎታትን በመጠበቅ ከታመንን ኅሊናችን ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን ከማሰብ አያቆምምና ለብ ያልን ከመሆን እንድናለን።

ከመንፈስ ዝለት ምክንያቶች መካከል የሚመደበው ከእግዚአብሔር ርቆ ለረጅም ጊዜ መቆየት ነው። ለዚህ የተጋለጡ ሰዎች የነግህና የንዋም ጸሎትን ብቻ በመጸለይ በመሐል ግን ምንም ጸሎት የማያደርሱት ናቸው። እነዚህ በመሐል የሚገኙት ጊዜያት ግን እንዲያውም ፈተናና መሰናክል የሚበዛባቸው ናቸው።

ከመንፈስ ዝለት ለማምለጥ ከፈለግን በየጊዜው ልባችንን ወደ እግዚአብሔር እያቀናን አንድ ደቂቃ አልያም ጥቂት ሰከንዶችን የሚወስድም ቢሆን አጭር ጸሎት ማድረስ ይገባናል።

## *ከንስሐ ርቆ መገኘት*

በመንፈስ ንቁ ሆነው የሚገኙ ሁለት ዓይነት ሰዎች ናቸው:: የመጀመሪያው በቅርብ ንስሐ የገባ ሰው ነው:: ይህ ሰው ትሑትና የተረጋጋ ነው:: እንባው ቅርብ ነው:: በከንቱ ያለፈውን የቀደመ ጊዜውን ለመካስ ቆርጦ ስለተነሣ መንፈሳዊ ትጋት ያለው ነው::

ሁለተኛው ደግሞ ፍቅረ እግዚአብሔር የተዋሐደው ነው:: ይህ ሰው ደግሞ ፍቅር በልቡ ውስጥ እንደሚነድ እሳት ነው:: ይህም በጸሎቱ፣ በአገልግሎቱ እንዲሁም በማንኛውም መንፈሳዊ ሥራው የሚገለጥ ነው::

ከነዚህ ከሁለቱ መሐል የሚገኝ ግን ለብ ያለ ነው:: በበረሃ ይንከራተቱ የነበሩ እስራኤላውያንን ይመስላል:: ልቡናው ከባርነት ምድር ቆርጦ አልወጣም ደግሞም ወደ ምድረ ርስት ከነዓን አልገባም::

*ለብ ያለ ሰው:-*

- በንስሐ ወይም በፍቅር በኩል የሚያሳየው ምንም ፍሬ የለም:: በሩቅ ቆሞ ዐይኑን እንኳን ለማንሳት እንደፈራው ቀራጭ ያለ የመንፈስ መቃጠልም /ሉቃ. 18÷13/ ሆነ በፍቅር ሆኖ የጌታችንን ደረት እንደተደገፈው ቅዱስ ዮሐንስ ያለ ፍጹም ፍቅር የለውም::
- ስለኃጢአቱ ያለቀሰባቸው ቀኖች ይናፍቃቸዋል:: ነገር ግን ሊያገኛቸው አይችልም::
- ይጸልያል፣ ይጾማል፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያነባል፣ ጉባዔያትን ይሳተፋል፤ ይናዘዛል፣ ይቆርባል፣ ያገለግላል፣ ነገር ግን በዚህ ሁሉ መሐል ልቡን ትሑት ለማድረግ የሚገፋፋው ነገር አያገኝም::
- ከመንፈሳዊነት ርቆ ስለሄደ ልቡናው መውቀሱን በማቆሙ የሚሠራው ሥራ የማይገባ መሆኑን እንኳን አያውቅም:: ዕንባውን ወይም ቅናቱን አጥቷል:: ነገር ግን ያለፍቅር በመንፈሳዊ ተግባራት ይሳተፋል::

### *መፍትሔ*

- በመንፈሳዊ ደረጃቸው ላቅ ካሉ ሰዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመመሥረት አልያም የቅዱሳንን ገድል በማንበብ ራሱን ሊመረምር ይገባዋል:: በዚህም የርሱን ደረጃ አነጻጽሮ ወደ ንስሐ ሕይወት እንዲመለስ ይሆናል::
- በሌላ በኩል የቀደመ መንፈሳዊ ሕይወቱን የሚመልሱለትን መንፈሳዊ ምግባራት መሥራት መቀጠልና ድካሙን ተረድቶ ወደንስሐ ሊመለስ ይገባዋል::



- በጸሎቱ፣ በጾሙና በሌሎቹም ምግባራት ሁሉ መንፈሳዊ ሰው ለመሆን መጣር ይኖርበታል::

ይህም መንፈሳዊ ተግባራትን ከልማድ አንፃር ሕግን ደንብን ለመፈጸም ከሚል ከንቱ ጉዞ አላቅቆ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዲኖረው ያደርገዋል:: በዚህም ጊዜ ከራሱ ጋር በእውነት መክሮ ጾሙ፣ ጸሎቱ ሌላውም ሥራ የሚገባውን ያህል እንዳልሆነ ይረዳል:: በመሆኑም ለጸሎቱ፣ ለጾሙ፣ ለንባቡ ለሌሎችም መንፈሳዊ ተግባራት የሚሆን አዲስ መንገድ መቀየስ እንዳለበት ይሰማዋል::

በዚህም ጥሩ የንስሐ ሕይወት ይጀምራል:: ይህም ከመንፈስ ድካም አላቅቆ በቀጥታ ወደ መንፈሳዊ ትጋት ይመራዋል::

- በቀደመው ጊዜ ንስሐው በጠንካራ መሠረት ላይ ባለመመሥረቱ ወደ ድካም መርቶት ይሆናል:: ስለዚህም እውነተኛውን መንፈሳዊ ሕይወት ለመምራት የሚያስችለውን የንስሐ መንገድ ይጠርጋል::
- ምናልባት ለንስሐ የሚያነሣሣው ከውስጡ ያለው ስሜት በመጥፋቱ ለድካም ተጋልጦ ይሆናል:: ስለዚህም ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት በፍቅር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ለማድረግ መጣርና የመንፈሳዊ ሕይወትን ጠቀሜታ መረዳት መቻል አለበት:: ይህም ከድካም እንዲላቀቅ ያደርገዋል::
- ለንስሐ ተነሣሥቶ ንስሐ መግባት ብቻውን በቂ አይደለም:: በዚህ ሳያቆም ይህ መነሣሣቱ ለሁልጊዜ እንዲቀጥል ለማድረግ መጣር ይኖርበታል::

### *በጥቂት ነገር መርካት*

መንፈሳዊ ሰው መሻሻል እያሳየ በሄደ ቁጥር መንፈሳዊ ስሜቱና ፍላጎቱም ይጨምራል:: ምክንያቱም መንፈሳዊ ጉዞ ማለት በመንፈሳዊ ሕይወት እያደጉ መሄድ ነው::ነገር ግን በአንድ በተወሰነ ደረጃ ላይ መንፈሳዊ ተግባራትን ባቆምን ጊዜ የመንፈስ ዝለት ይከተላል::

ብዙ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ችግር ይገጥማቸዋል:: ከንስሐ በፊት ከጸሎት ጋር ብዙም ያልተለማመዱ ሰዎች ከንስሐ በኋላ ጸሎትን በማድረስ የጸሎትን ጣዕም ሲቀምሱ ልባቸውን በመንፈሳዊ ሐሴት ይሞላሉ::

እነዚህም ሰዎች በጸሎት ረገድ የተወሰነ ደረጃ በደረሱ ጊዜ ስለሚያቆሙ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ድካም ይመጣባቸዋል::

ይህም በሌሎች መንፈሳዊ ተግባራትም ሲንጸባረቅ እናያለን:: ለምሳሌ በጾም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ እና በመሳሰሉት::

እነዚህን ሰዎች ስናስብ የመኪና ነገር ትዝ ይለናል:: በእንቅስቃሴ ላይ በሆነ ጊዜ ሁሉ ሙቀት ይሰማዋል:: ነገር ግን ለረጅም ጊዜ ከቆመ ባትሪው ስለሚደክም እንደገና መሞላት ይኖርበታል::

እስከ ሦስተኛው ሰማይ ተነጥቆ የነበረውን ቅዱስ ጳውሎስን እንመልከት:: /2ቆሮ. 12÷2/ «አሁን እንዳገኘሁ ወይም ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም:- ነገር ግን...ያን ደግሞ አይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ::» /ፊልጵ. 3÷12 - 14/ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ያለ ትልቅ ሐዋርያ እንዲህ ለበለጠ ነገር የሚታገል የሚፈጥን ከሆነ እኛስ ምን ልናደርግ ይገባናል?

ለሚመጣው ነገር የምንታገል ከሆነ አንድ የተወሰነ ደረጃ ላይ ቆመን እርካታን አናገኝም:: ስለዚህም እንቅስቃሴያችን ስለሚቀጥል በድካም ከመውደቅ እንድናለን:: ብንወድቅም እንነሳለን ጉዟችንም ይቀጥላል::

መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ማቆም የራሱ የሆኑ አደጋዎች አሉት:: ምክንያቱም ወደ ድካም ብቻ ሳይሆን ወደ ውድቀት ይመራናልና ነው::

መንፈሳዊነት የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ያለበት ሕይወት ነው:: የማያቋርጥ መሻሻል የሚታይበት፣ ዓላማው ፍጹምነት ለማግኘት መፍጠን ነውና::

እምነተ ፅኑ ሰው በመንፈስ መኖርን ብቻ በቃኝ ማለት የለበትም:: የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ገንዘቡ ለማድረግ መፍጠን አለበት:: «መንፈስ ይሙላባችሁ» /ኤፌ. 5÷18/ ይህ ሙሉነት ከድካም /ዝለት/ ይጠብቀናልና::

## በመንፈሳዊ ሕይወት የኃላፊነት ቦታዎች አደጋ

አንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወትን ሲጀምር ትሑትና ራሱን ያዋረደ ስለሆነ ጸጋ እግዚአብሔር አይለየውም:: እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነውና:: /መዝ. 33÷18/ልቡ ትሑት የሆነ ሰው መንፈሳዊ ስሜቱና ፍላጎቱ ከፍ ያለ ነው::ይህ ሰው ከጊዜ በኋላ መሻሻል እያሳየ ሲሄድ የተወሰኑ ኃላፊነቶች ይጣሉበትና የኃላፊነት ቦታዎችን መያዝ ይጀምራል::

ይህ የተሾመበት ቦታ በራሱ አደገኛ አይደለም:: ነገር ግን ራሱን ከፍ ከፍ ሲያደርግ ፣ባለሥልጣንነት ሲሰማው ፍቅርና ትሕትናን ያጣል:: ይህም ወደ መንፈስ ዝለት ይመራዋል::

ኃላፊነት የተሰጠው ሰው በመጀመሪያ ንስሐ ገብቶ ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጣ «ጌታ ሆይ ከዚህ ውብ ኅብር ውጭ ነኝ:: ከነዚህ ቅዱሳን ኅብረት ልደመር አይገባኝም:: በዚህ ቦታ መሆን የማይገባኝ



ነኝ:: እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ» /መዝ. 5÷7/ እያለ ነበር::

የኃላፊነት ቦታ ከተሰጠው በኋላ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደው ለማስተማር፣ ነገሮችን ለማደራጀትና ለማስተዳደር ይሆናል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባም እንደተለመደው የማይገባኝ ነኝ እያለ አይደለም:: ተሳልሞ መግባትን እንኳ ይረሳል::ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደው ለዚህ ወይም ለዚያኛው ሰው ትእዛዝ ለመስጠት፣ ለመገሰጽ ወይም ስለአንድ ጉዳይ ለመወያየት፣ አንዳች ዓይነት ሥራ ለመሥራትና በኃላፊነት የተቀመጠበትን ሥራ ለመሥራት ብቻ ነው:: በዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔርንና በእግዚአብሔር ቤት መኖሩን ይረሳል::

የቀደመው «ከዚህ ከተዋበ ኅብር ውጭ ነኝ» የሚለው ንግግሩ ፈጽሞ ጠፍቷል:: ቤተ ክርስቲያን በእይታው የነበራትን ክብር አጥታለች:: በቤተ ክርስቲያን ሆኖም ከአንዱ ጋር ያወራል፣ ከባልንጀሮቹ ጋር ይስቃል:: የፈለገውንም ሰው ለቦታው ምንም ክብር ሳይሰጥ ከፍ ባለ ድምፅ ይጣራል::

የመንፈስ ዝለቱም እያደገ ይሄድና ለጸሎትና ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሁሉ ያለውን ክብር እስከማጣት ያደርሰዋል:: ጸሎታት በቃሉ የያዛቸው፣ ትርጉማቸውን በጥልቀት ያወቃቸው ቃላት የተቀነባበሩበት ተራ የሙዚቃ ኖታዎች ይሆኑበታል:: ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሪያ መሆኑ ሁሉ ይቀራል::

ከዚህ የበለጠ የመንፈስ ዝለት ምንድነው? የሚያስደንቀው ደግሞ ይህ ሰው ምናልባት ፍርሃትን አውልቆ የሚጥል ፍጹም ፍቅር አግኝቻለሁ ብሎ ምክንያት ሲሰጥ ነው:: /1ዮሐ. 4÷18/ የዚህ ሁሉ መጨረሻው አክብሮትን፣ ትሕትናን፣ ራስን ማዋረድን በማጣት በትዕቢት መውደቅ ነው::

## መፍትሔ

- ራሳችንን ከቤተ ክርስቲያን ምሰሶዎች እንደ አንዱ አድርገን አንገምት::
- በጣም አስፈላጊ ሰው ከመሆናችን የተነሣ እኛ ብንቀር የማይሞላ ባዶ ቦታ የምንተው መስሎ አይሰማን::
- ምናልባት በኃላፊነት ካሉ ሰዎች ጋር አለመግባባት ቢፈጠር የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚነቀነቅ መስሎን ከአገልግሎት እለቃለሁ ብለን ለማስፈራራት አንሞክር:: ከዚህ ሁሉ መጋረጃ በስተጀርባ ድብቅ ትዕቢት እንዳለ እንወቅ::

ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ያለ እኛም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ሆና እንደምትቆይ ሊያስገነዝበን እግዚአብሔር ከአገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ያግደናል፡፡ ይህ ወደ ቀደመ መንፈሳዊ ፍቅራችን እንድንመለስ ያደርገናል፡፡

ታላቁ ነቢይ ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የበአል ነቢያትን ድል ነስቶ ካስወገዳቸው በኋላና ለማያትንም በጸሎቱ ከሰገመ እንዲሁም ከከፈተ በኋላ «እዚያም ወዳለ ዋሻ መጣ፥ በዚያም አደረ፤ እነሆም :- ኤልያስ ሆይ:- በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል የእግዚአብሔር ቃል ወደ እርሱ መጣ፡፡ እርሱም:- ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና፤ እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ፤...አለ፡፡» /1 ነገ.19፥ 9-11/ ነገር ግን እግዚአብሔር ለበአል ጉልበታቸውን ያላንበረከኩ ሰባ ሺህ ሰዎች እንዳሉ አሳየው፡፡

እኛም በቤተ ክርስቲያን የኃላፊነት ቦታ ላይ ከተሾምን እኛ ከኃላፊነት ከወረድን ቤተ ክርስቲያን ሕልውናዋ የሚቆም መስሎ ሊታየን አይገባም፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ ኤልያስ «እኔ ብቻዬን ቀርቻለሁ» ቢልም እርሱ የማያውቃቸው እንደርሱ እግዚአብሔርን ብቻ የሚመልኩ ሰዎች እንዳሉ አሳይቶታል፡፡ በተጨማሪም «ሄድ በመጣህበትም መንገድ...ተመለስ፤...በፈንታህም ነቢይ ኑሆን ዘንድ...የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው፡፡» /1ነገ19፥15- 16/ ለለው፡፡ ነቢዩም እኔ እያለሁ እንዴት ሌላ ሰው ይሾማል? ምን አድርጌ ነው? በማለት አላጉረመረመም ፡፡ ይህም ለታላቅ ክብር አብቅቶታል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ እርሱ በእሳት ሠረገላ ከተነጠቀ በኋላ ኤልሳዕም የኤልያስን መንፈስ እጥፍ ተቀበለ፡፡ ከኤልያስም የበለጠ ተአምራትን ሠራ፡፡ ምድርም ከኤልያስ በኋላ እንደነበረች ቆየች ፡፡ ይህ ሁሉ ግን ወደ ሰማይ የተነጠቀውን በታቦር ተራራም ላይ ለምስክርነት የተጠራውን የታላቁን ነቢይ ክብር አልቀነሰውም፡፡

እግዚአብሔር በፍላጻ ማህደሩ ውስጥ ብዙ ቀስቶች አሉት፡፡ ከድንጋዮችም ለአብርሃም ልጆችን ሊያሥነሣ ይቻለዋል፡፡/ማቴ.3፥9/ ስለሆነም እኛም በቤ.ክርስቲያን ኃላፊነት ላይ በተሾምን ጊዜ እኛ ከሌለን ምንም ሥራ የማይሠራ የማይሞላ መስሎን ሊታየን አይገባም፡፡

ስለዚህም እግዚአብሔር ለአገልግሎት ከሾመን «ጌታዬ ሆይ አንተን ከሚያገለግሉህ ጋር እኩል ትቆጥረኝ ዘንድ እኔ ማን ነኝ? እኔ አፈ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ፡፡ /ዘፀ. 4፥10/ ምናልባት የማሰናከያ ዐለት ልሆን ኃላፊነቴን በአግባቡ ላልወጣ እችላለሁ፡፡ በርግጥ ከኔ የተሻሉ ሌሎች አገልጋዮች ቢኖሩህም እኔን ለማበረታታት ስትል ብቻ ሳይገባኝ በወይን ተክል ቦታህ ቀጥረኸኛል» ልንለው ይገባል፡፡



እንዲህ ባለ ትሑት መንፈስ ሆነን ስንገኝ ነው በተቀመጥንበት ኃላፊነት ሆነን የመንፈስ ድካም የማያጠቃን፡፡ ሰዎች በሚያደንቁን ጊዜ ኃጢአታችንንና ደካማ ጎናችንን ስናስብ የበለጠ ድካም ከኛ ይርቃል፡፡

ማንኛውም ዓይነት ውዳሴና አድናቆት ጸጋ ተለይቶን እንዳይሄድና መንፈሳዊ ትጋታችን እንዳይቀዘቅዝ ወደ ውስጣችን ዘልቆ እንዲገባ አንፍቀድለት፡፡ ከዚህ ይልቅ ምስጋናን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት እንደ ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ» /1ቆሮ. 15፥10/ ልንል ይገባል፡፡

አለቃ ሆነን ወደነዚህ የኃላፊነት ቦታዎች ከተቀመጥን በፊታችን እነዚህን መመሪያዎች ማስቀመጥ አለብን፡፡ እነርሱም:-

1. ከአምላኪነት ወደ ምሁርነት እንዳንቀየር መጠንቀቅ፡፡
2. በዓለም ወጀብ ወይም በፍልስፍና ተጠርገን እንዳንወሰድ መጠንቀቅ፡፡
3. ዕውቀትንም ለማወቅ ብቻ ወይም የዕውቀት ምንጭ ለመሆን ብቻ አንፈልጋት፡፡ ምክንያቱም በዕውቀት መሐል ጸጋ መንፈስ ቅዱስን መርሳት አለና በመጻሕፍትና በንባብ ተማርከን ራሳችንንና ዘላለማዊ ሕይወትን ልንረሳ እንችላለን፡፡
4. በክርክር በመጠመድ፣ በብዙ ክርክሮች ተሣትፈን ለሌሎች ያለንን ፍቅር እንዳናጣ መጠንቀቅ ያሻል፡፡ ምክንያቱም ትኩረታችን ለማሸነፍና በሌሎች ላይ የበላይነትን ለማግኘት ብቻ ስለሚሆን ነው፡፡

ምናልባት ራሳችንን ከፍ ከፍ በማድረግ በውይይቱ ወቅት ሌሎችን ልንጎዳ ልናቋሽሽ እንችላለን፡፡ ወይም በራሳችን በመተማመን እኔ ያልኩት ካልሆነ ብለን የሌሎች ሃሳብ የማንቀበል ግትር እንሆናለን፡፡

የዕውቀት ጎተራ የሆኑ ነገር ግን መንፈሳቸው ባዶ የሆነ ብዙዎች ናቸው፡፡ ከሕይወት ጋር የተጣመረ ጥቂት ዕውቀት ያለምንም ሥራ ከተያዘ ሠፊ ዕውቀት የተሻለ ነው፡፡ ዕለት ተዕለት የተወሰኑ ምዕራፎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ያለምንም ማስተዋል ብናነብ ጥቅሙ ምንድነው?

በመሆኑም ብዙ ብናነብም ሕይወታችን ግን ደካማ እንደሆነ ይቀራል፡፡ ዋናውና አስፈላጊው ነገር ብዙ ንባብ ሳይሆን በማስተዋል ማንበባችንና በሕይወት መተርጎማችን ነው፡፡

የኃላፊነት ቦታዎችን አንፈልግ፣ በአስተዳደርም ሆነ በመሪነት ደረጃ ራሳችንን ገዞቅ አድርገን ምንም እንደማናውቅ እንገምት የማናውቃቸውን ጉዳዮችንም በተመለከተ «አላውቅም» ማለት እንደማያሳፍር እንረዳ፡፡

## ለሌሎች ብሎ መሥራት

ክርስቲያናዊ ሕይወት ስንጀምር ሕይወትን እንኖር የነበረው ከፊታችን ዘላለማዊነትን አስቀምጠን፣ በእግዚአብሔር ፍቅር ተነሣሥተን ነበር:: ነገር ግን እየቆየን ስንሄድ ሌሎች ወደ ሕይወታችን ይገቡና የዓላማችን አንዱ ክፍል ይሆናሉ::

ዋናው የእኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለሌሎች ምሳሌ ለመሆንና መሰናከያ ላለመሆን ብቻ ይሆናል:: በዚህ ወቅትም በጎ የምንሠራው ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተነሣ ሳይሆን ለሰዎች ምሣሌ፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት ሕያው ናሙና ለመሆን ወይም በጨለማ ይመላለሳሉ ለምንላቸው ሰዎች ብርሃን ለመሆን ነው::

በተመሳሳይም ኃጢአት የማንሠራው ኃጢአትን በመጥላት ሳይሆን ለሌሎች የማሰናከያ ዐለት ላለመሆን ነው:: እንዲያውም ሌሎችን እስካላሰናከልን ኃጢአትን መቃወማችን ይቀራል::

ስለዚህ መንፈሳዊነታችን ከውስጥ የመነጨ ሳይሆን ውጫዊ ስለሚሆን እንዝላለን፤ወደ ሁለት ባሕርያት ባለቤትነትም እንለወጣለን:: አንዱ ለሰዎች መሰናከል እንዳንሆን ሲያስጠነቅቀን ሌላው ደግሞ እስካላዩን ድረስ ኃጢአትን እንድንሠራ ያደርገናል::

ሰዎች እኛ የተናገርነውንና የምንሠራውን እንዴት እንደሚመለከቱት የማወቅ ጉጉት ያድርብናል:: ይህ እያደገ ሲሄድም ሰዎች የሚያስደስታቸውን ጥቂት በጥቂት እየሠራን በስተመጨረሻም ዓላማችን ሁሉ ሰዎችን ማስደሰት ይሆናል:: መንፈሳዊ ዓላማችን የበቃለትና በመንፈስ የዛልን ሆነን እንገኛለን::

በስብሰባ (በጉባዔ) ወቅት ጸሎት ስናደርስ ዋናው ሃሳባችን የሚሆነው በዚያ ያሉት ስለጸሎታችን ምን እንደሚያስቡ ስለሚሆን ጸሎታችን ለእግዚአብሔር አይደለም:: እንዲያውም በጸሎት ጊዜ እንባ ልናነባ እንችላለን:: ከእግዚአብሔር ፍቅር የመነጨ ቢሆን ምንኛ መልካም ነበር? ነገር ግን ሃሳባችን ሰዎች የእኛን መንፈሳዊነት እንዲያደንቁ እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር በማስብ አይደለም::መነኩሲቷ እናታችን ሣራ «እያንዳንዱን ሰው ለማስደሰት የምጥር ከሆነ በእያንዳንዱበር በማንኳኳት መንገዴን እስታለሁ» በማለት የተናገረችውን ልናስብ ይገባል::

ለሌሎች ሰዎች ታዛዥ በመሆን ብቻ መንፈሳዊ ሕይወታችን ሊደክም ይችላል:: ለሰዎች ስንል ምንም ጥቅም በሌላቸው ነገሮች ጊዜያችንን እናጠፋለን:: በጣም አስጨናቂ ወደሆኑ ጉዳዮች ውስጥ እንገባለን:: በእነርሱ ምክንያት ጸሎታችን ሊታጎል ሊዘገይ ይችላል:: ስለዚህ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ቃል ገንዘብ ልናደርግ ይገባል:: «....ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ



ባሪያ ባልሆንሁም» /ገላ.1÷10/ስለዚህ በመንፈስ ዝለት እንዳንጠቃ ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት በመንፈሳዊ ሚዛን ልንመዝነው ይገባል::

## መንፈሳዊ ተግባራትንና የጸሎት ሰዓታትን መዘንጋት

ከሌሎች ምክንያቶች በተጨማሪ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚታየው የመንፈስ ዝለት የሚፈጠረው መንፈሳዊ ተግባራትንና የጸሎት ሰዓታትን በመዘንጋት ነው:: ምክንያቱም እነዚህ ምግባራት ስለእግዚአብሔር እንድናስተውል፣ ለመንፈሳዊ ሥራዎች እንድንነሳሳና ልቦናችንም እንዲፀና የሚያደርጉ ስለሆኑ ነው:: እነዚህን ስንዘነጋ ደካማና ልፍስፍስ እንሆናለን::

መንፈሳዊ ተግባራት ያልናቸው:- ጸሎት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፣ ጾም፣ ንስሐ መግባት፣ ቅዱስ ቁርባን መቀበል፣ መንፈሳዊ ጉባዔያት መሳተፍ ነው:: እነዚህ ሁሉ ከልብ በመነጨ መንፈሳዊነት ሊተገበሩ የሚገባቸው ናቸው::

ምናልባት «እነዚህን ሁሉ እፈጽማለሁ:: ነገር ግን አሁንም ለብ ያልኩ ነኝ:: ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? መፍትሔዎቹስ?» ብለን ልንጠይቅ እንችላለን:: መልሱም እንደሚከተለው ይሆናል::

1. ጸሎት የምናደርሰው፣ መንፈሳዊ ተግባራትን የምንፈጽመው እንደ ልማድ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህም ከልብ ሆነን በመረዳት፣ በጥልቅ ስሜት ልንተገብራቸው መጣር አለብን::
2. አልያም ከውጭ የመጣብን ጦርነት አለ ማለት ነው:: በዚህም ጊዜ ከዚህ ውጊያ የምንወጣበትን ኃይል ሰጥቶ እግዚአብሔር እስኪታደገን ድረስ ትእግሥት ያስፈልጋል:: ጎን ለጎን ግን መንፈሳዊ ተግባራቱን ማቋረጥ የለብንም::

ይህንንም ለመቋቋም ከሚያስችሉ መንፈሳዊ ተግባራት አንዱ የጸሎት ሰዓታትን መጠበቅ ነው:: የጸሎት ሰዓትን የሚጠብቅ ሰው በሚጸልየው ጸሎት ልቡናው ለትሩፋት ይነሣሣል::

በጸሎት የጠየቅነው ጥያቄ ቶሎ መልስ ካላገኘ ተስፋ መቁረጥ የለብንም:: ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩና በምስጋናው «ከማለዳው ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች» /መዝ. 129÷6/በማለት ተናግሯል:: ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ስንቆም መልስ እስከምናገኝ ከማለዳ ጀምሮ እስከ ሌሊት ልንታገስ ያስፈልጋል::

## *መንፈሳዊ ሕይወትን እንደተራ ነገር አድርጎ መገመት*

አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወትን ማለትም መጸለይ፣ መጾም፣ ንስሐ መግባት፣ ቅዱስ ቁርባን መቀበል፣ ጉባዔ መሳተፍ ተራ ነገር አድርገው ይገምታሉ። እነዚህንም ለመሥራት የጊዜ ሰሌዳ አውጥተው ልቡናቸው ብቻ እንዳይወቅሳቸው ይሠራሉ። ነገር ግን የሚታዩት በመንፈስ ሲዝሉ ነው። ምክንያቱ ምን ይሆን?

- ራሳችንን በእነዚህ ተግባራት ብቻ ወስነን የመንፈሳዊ ሥራዎች ሁሉ መነሻ የሆነውን የልብ ንጽሕናን ዘንግተን ይሆናል።
- ከመንፈስ ፍሬዎች የተለየ ተራ መንፈሳዊ ተግባር እንደ ፈሪሳውያን የልቦናችንን ጡንቻ አሳብጠት ይሆናል።

እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎች ውጪው ነጭ የተቀባ መቃብርን ይመስላሉ። ልቡናቸው ከእውነተኛ መንፈሳዊ ስሜት የተለየ ሲሆን ለአፍአዊ ተግባራት ግን የሚጠነቀቁ ፈሪሳውያንን ይመስላሉና።

ስለዚህ በውስጣዊ ነገሮች እና ዐበይት ሥነ ምግባራት በሆኑት ፍቅር፣ እምነት፣ ትሕትና፣ ቅንነት እና ንጽሕና ላይ ልናተኩር ያስፈልጋል። ይህን ካደረግን ጸሎታችን በእግዚአብሔር ፍቅር ከተመላ ልብ እንደሚወጣ ነበልባል ይሆናል።

አንዳንድ ሰዎች በመካከላቸው መረረ ጠብ እያለ ለጸሎት ይቆማሉ። በጣም ጸያፍና ከንቱ ድካም ነው። ልባቸው በጥላቻ፣ በቁጣ፣ በትዕቢት እና በመሳሰሉት ተሞልቶ ጸሎት ያደርሳሉ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ያነባሉ፣ ይሰብካሉ። ልቡናችን ከመንፈስ ተለይቶ ሳለ ጸሎት እንዴት ጥልቅ ይሆናል? እንዴት ሆኖ ጸሎታችን ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኘናል? ልቡናችን ውስጥ ያለው ቁጣ፣ ተንኮል፣ ክፉ ሃሳብ ብቻ ነውና።

የመንፈስ ዝለትን ለማስወገድ ከፈለግን መንፈሳዊ ሥራችንን በመንፈስ ፍሬዎች ላይ የተመሠረቱ ማድረግ አለብን። /ገላ. 5÷22/

በሥራችን ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ «ልጄ ሆይ÷ ልብህን ስጠ ኝ» /ምሳ.23÷26/በማለት ልባችንን እንድንሰጠው ይፈልጋል።አይሁድንም እንዲህ በማለት ገሥጿቸዋል። «እጃችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዐይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ ÷ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፤ እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል። /ኢሳ. 1÷15/

## *በሕይወት ውስጥ ያለ ከንቱ ምኞት*

አንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወትን እንደ ጀመረ በትክክል ሊጓዝ ይችላል። ለተወሰነ ጊዜም በዚሁ ይቀጥላል። ከዚያም ከንቱ ምኞት ወይም የዓለም ፍቅር ልቡናውንና ስሜቱን በመቆጣጠር በእግዚአብሔር



ተይዞ የነበረውን ቦታ በመውሰድ ወደ ዝለት ይመራዋል። ለአምላኩ የነበረውን ፍቅር በተወ ጊዜ መንፈሳዊ ፍላጎቱ ቀንሶ ለብ ያለ ሕይወት ይጀምራል።

ስለዚህ በልባችን ውስጥ የእግዚአብሔር የነበረውን ቦታ የወሰደ እንግዳ ነገር ምን እንደሆነ እንመርምር። በድብቅም ይሁን በግልጥ ልባችን ውስጥ የገባ ኃጢአት ካለ ምን እንደሆነ ለማወቅ መጣር አለብን። ምክንያቱም ኃጢአት የበግ ለምድ ለብሶ ወይም መልካም በሚመስለን ነገር ተመስሎ ገብቶ ሊሆን ይችላልና።

ኃጢአት እንደ ቅናት፣ እውነትን መግለጥ፣ ፍቅር እና በመሳሰሉ ነገሮች ተመስሎ ሊመጣ ይችላል። እነዚህን የምንሠራው ባለመረዳት ከሆነ ማለት ነው።

እውነትን ለመመስከር በሚል ሽፋን ተከልሎ አንድ ሰው ሌሎችን በጠላትነት መንፈስ ሲዘልፍ ያለርኅራኄ ሲወቅስ ይታያል። ለውጥ ለማምጣት በሚል ሽፋን ሌሎችን ይተቻል፣ ይኰንናል፣ እንዲያውም ሊሳደብ ይችላል። ቀስ በቀስም ያገኘውን እንደሚበላ እሳት ጨካኝ ይሆናል። ሁሉን የሚጠራጠር፣ በሐሰት ሁሉን የሚወነጅል፣ በሰዎች ላይ ምንም መልካም ነገር የማያገኝ የትችት መሣሪያ ወደ መሆን ይቀየራል።

ይህ ሰው እንክርዳዱን (ገለባውን) የሚያጠራ ሊመስል ቢችልም እርሱ ራሱ እንክርዳድ እየሆነ ነው። በሕይወቱ ውስጥ ምንም መንፈሳዊ ነገር ስለማይገኝ ወደ መንፈስ ዝለት ያመራል። «ከአፌ ልተፋህ ነው» /ራእ. 3÷16/ የሚለው የጌታ ቃል የተነገረው ለእንደዚህ አይነቱ ሰው ነው።

እንደዚህ ማለትም አንድ ሰው ለማሻሻል ከመጣር፣ ቅናቱን ከማሳየት ወይም እውነትን ከመደገፍ ማቆም አለበት ማለታችን አይደለም። ነገር ግን ይህን ሁሉ ከልብ በመረዳትና በጥበብ ሆኖ በመንፈሳዊው መንገድ ሊያደርገው ይገባል ማለት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ «በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን» /1ቆሮ. 16÷14/ ዳግመኛም «ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማነው? በመልካም አኗኗሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ። ነገር ግን መራራ ቅናትና አድመኝነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ አትመኩ፤ በእውነት ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም» /ያዕ. 3÷13-15/ በማለት ይመክረናል።

የደከመ ሰውን የማቅናት መንፈስ በፍቅር፣ በትኅትናና በጥበብ ከሆነ የዚህ ሰው ቅናት በትክክለኛው መንገድ ያለ ሲሆን የመንፈስ ዝለትም አያጋጥመውም።

ሌሎችን ስለማቅናት የተናገራቸው የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቃላት ምንኛ ያማሩ ናቸው? « ... መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም።» /ገላ. 6÷1፣2/

ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወትን ሲጀምሩ የሚያሳዩት መንፈሳዊ ስሜት ከመሆኑ የተነሣ ሌሎች የሚያዩአቸው በአድናቆት ለአገልግሎት ያጯቸዋል። ወደ አገልግሎት ሲገቡ ለእግዚአብሔር ቅናት አላቸው። ግን ያለ ዕውቀት ነው። /ሮሜ. 10÷2/ በመሆኑም የመንፈስ ዝለት ያጋጥማቸዋል።

በእውነት ሌሎችን ለማቅናት (ለማሻሻል) በሚል ነገር ብቻ የተጠመዱ ብዙዎች ጠፍተዋል። ሌሎችን ለማቅናት የሚኖር ሰው ሁል ጊዜ የሚያስበው ስለራሱ ኃጢአት ሳይሆን ስለሌሎች በመሆኑ ይዝላል። በመጀመሪያ ንስሐ ሲገባ ስለራሱ መንፈሳዊነትና ድኅነት ያስብ ነበር። በኋላ ግን በአገልግሎት ውስጥ ጨርሶ ራሱን በመዘንጋት ስለሌሎች ድኅነትና መሻሻል፣ ስለሌሎች ኃጢአት ብቻ ያስባል። ይህንንም ቢሆን በተገቢው መንገድ አያደርገውም። ከፍቅር በተለየና ድብቅ ትዕቢትን በተላበሰ መንገድ እንጂ።

እንዲህ ያለው ሰው የድካሜ ምክንያት ምንድነው? ብሎ ቢጠይቅ መልሱ አሁን ያመጣው አዲስ ጠባይ ነው። በትሕትና ሆኖ የራሱን ድኅነት እያሰበ ቢኖር ከሁሉ የበለጠ ነው።

ክርስቲያኖች! ስለራሳችን እናስብ! በመንፈስ ስለዛሉ ስለሌሎች ከማሰባችን በፊት እኛ መታደስ (ንስሐ መግባት) ያለብን ኃጢአተኞች አይደለንምን?

ሌላው ልናነሣው የሚገባው ነገር ቢኖር ደግሞ ከቅናት የተነሣ ሌሎችን አቀናለሁ ብለን እንነሣ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ያላወቅነው ጨካኝነት በልባችን ሊኖር ይችላል። መንፈሳዊ ሕይወትን ስንጀምር ይህ ጭካኔ በሥውር ገብቶ በኋላ በቅናትና ሌሎችን ማቅናት በሚል መንፈስ መገለጥ ይጀምራል።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎስ «...ዝለፍና ገሥጽ ምከርም።» /2ጢሞ. 4÷2/ ነው ያለው። እርሱ ራሱ ግን ይህን እንዴት ይፈፅም ነበር? ከሚሊጢን ልኮ ያስጠራቸውን የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት እንዲህ አላቸው «ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በዕንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥኩ እያሰባችሁ ትጉ።» /የሐዋ. 20÷31/ ቅዱስ ጳውሎስ ከመገሠጽ ያልደከመበት ምክንያት ግሣጼው ከእንባ ጋር ስለነበር ነው። በተግሣጹም ውስጥ ፍቅርና አክብሮት ነበረበት።



የልብ ጭካኔም ሆነ ሌሎችን መኮነን የመንፈስ ዝለት ምክንያቶች ናቸው። በሁለቱም ውስጥ ጸጋ እግዚአብሔር ከዚያ ሰው ይለያል። ስለዚህም በመንፈስ መዛል ይገጥመዋል። ምክንያቱም መንፈሳዊ ቅናት የሰው ሥራ ሳይሆን በውስጣችን ካለ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅር ቢጽ የሚመነጭ ነው። በመሆኑም አንድ ሰው በጨካኝነትና በሌሎች ላይ በመፍረድ ከጸጋ በተራቆተ ጊዜ የመንፈስ ዝለት ያጠቃዋል።

## ትዕቢት

ትዕቢት ብዙ ዓይነት ነው።ምፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን «ትዕቢት ጥፋትን÷ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።» /ምሳ. 16÷18/ በማለት ትዕቢት ለመንፈስ ዝለት መንስዔ ከመሆኑም በላይ ወደ ጥፋትና ውድቀት እንደሚመራ ተናግሯል።

አንዳንድ ሰዎች ክርስትናን ገና ከመጀመራቸው ዓላማቸው ግቡን የመታ ይመስላቸዋል።ቶሎም ይረካሉ። ስለዚህም ድካም ይከተላቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች በተለየ መልኩ የታዘዙትን ሁሉ እየፈጸሙ «የማንጠቅም ባርያዎች ነን» /ሉቃ. 17÷10/ የሚሉ ደግሞ ሌሎች አሉ። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ገና ዓላማቸውን እየናፈቁ ስለሚኖሩ በመንፈስ ዝለት አይጠቁም። ምክንያቱም ከፍጹማን ማዕረግ ቢደርሱም «አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም፤ ነገር ግን ..... ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ...... በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ» /ፊልጵ. 3÷12፣13/ይላሉና።

ይህ ለበለጠ ነገር መፋጠን የመንፈስ ዝለትን ያስወግዳል። ሌት ተቀን ከረምት ከበጋ ለበለጠ ነገር የሚተጋ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከፍ ባለ ቁጥር ደካማ ጎኑ ብቻ ጎልቶ ስለሚታየው ድካም እንዳያገኘው ከመከላከሉም ባሻገር ዘወትር በመንፈስ እንዲቃጠል ያደርገዋል።/ሮሜ 12÷11/

ሌላው የትዕቢት ዓይነት ደግሞ አንድ ሰው ራሱን ከፍ ሌላውን ዝቅ አድርጎ የሚመለከትበት ነው። አዲስ ተነሣሂ በንስሐ መመላለስ በጀመረ ጊዜ ትጉህና የማይገባኝ ነኝ እያለ ይኖር ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ራሱን ከፍ ማድረግ ሲጀምር ጸጋ እግዚአብሔር ይለየዋል። ያኔ የመንፈስ ዝለት ይገጥመዋል።

መንፈሳዊ ቅናት ከትዕቢት ጋር በአንድነት አይመጣም። አንዱ ሲያይል ሌላው ቦታ ይለቃል።

በመንፈሳዊው ጸጋ የታደሉ ሰዎች ክርስቲያናዊ ሕይወት ሲጀምሩ በመልካም ሁኔታ ቢሆንም በኋላ ግን በትዕቢት ሲወጉ በመንፈሳዊ ሕይወት ይደክማሉ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካለው ፍቅር የተነሣ ጸጋውን ሁሉ ለሁሉም ሰው አይሰጥም። ምክንያቱም ሁሉም ሰው እንዲህ ያለ ጸጋን መሸከም ስለማይችል፣ አንዳንዶችም ሊታበዩ በኋላም ሊደክሙ ስለሚችሉ ነው።«እግዚአብሔር አንዳች ጸጋ ቢያድልህ ትሸከመው ዘንድ የሚያስችልህን ትሕትና አብረህ ጠይቀው። አለበለዚያ ግን እንዲወስደው ለምነው» ብለው አባቶች የተናገሩትም ለዚህ ነው።

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት «ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።» /መዝ. 118÷7/ ዳግመኛም «እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው» ይለናል። /መዝ. 33÷18/ በመሆኑም እግዚአብሔር እንዲቀርበንና ከድካም እንዲያላቅቀን ትሑት ልብ ሊኖረን ይገባል።

## የትሕትናን ጊዜ አሳጥሮ ለመደሰት መቻኮል

አንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ሲጀምር ትሑት በመሆኑ ስለኃጢአቱ ያለቅሳል። በዚህ ሁኔታ እያለ አንዳንዶች ጌታ ኃጢአቱን እንጂ ይቅር ስላለው ኀዘኑን አቁሞ እንዲደሰት ይመክሩታል። ስለዚህ ይህ ሰው ትሕትናውን ያቆማል። ጊዜ እያለፈም ሲሄድ መንፈሱ ይደክማል።

በትሕትና ያልተቃወምነው ኃጢኦት ተመልሶ ይመጣል። በዚህም ለብ ማለት ይከተላል።

ቅዱስ ጳውሎስ ከታላቅ መንፈሳዊነቱ እንፃር አልታበየም። ይልቅ የቀደመ ኃጢአቱን እያሰበ በትሕትና ይኖር ነበር። «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም»አለ። /1ቆሮ. 15÷9/

ቅዱስ ዳዊት ምሕረት እንደሚያገኝ ቃል ከተገባለት በኋላ፣ኃጢአቱ ሁልጊዜ በፊቱ ነበር። /መዝ. 50÷3/ ሌሊቱንም በሙሉ አልጋውን በዕንባው ያጥብ ነበር። /መዝ. 6÷6/

ቅዱስ ዳዊትና ጳውሎስ ልቡናቸውን ትሑት አድርገው በመጠበቃቸው በመንፈስ ዝለት አልተጠቁም። እኛም የመደሰት ሕይወት ለመምራት እንቸኩል። የምንደሰትበት ነገር ካገኘን «አይገባኝም» የመንፈስ ደስታ ቢሰማን እንኳ በልባችን ትሕትና ይኑረን።

## ቸልተኝነትና ለኃጢአት ቦታ መስጠት

እነዚህ ሁለቱ ወደ መንፈስ ዝለት እንደሚመሩ ግልጽ ነው። ከመንፈሳዊ ተጋድሎና ከፍጹምነት ጉዞ ተጻራሪ የሆኑ ነገሮች ናቸው። ለነዚህ የተጋለጠ ሰው በጸሎቱና በንቁነቱ እንዲሁም ቢ.አት.. በመቃወም በኩል ቸልተኛ ይሆናል። የእግዚአብሔር መንግሥ..



ለሰነፎች ሳይሆን ለተጋድሎ ለሚፋጠኑ የምትሰጥ ናት «የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን።» /ኤር. 48÷10/ ይላልና።

በአጠቃላይ የመንፈስ ዝለት የእምነትን መሠረት የሚነቀንቅ፤ በእግዚአብሔር ፊት በጥበብ ፣በቁመትና በሞገስ /ሉቃ.2÷52/ እንዳናድግ የሚያደርግ የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆ ነው።

ስለዚህ በክርስትና ሕይወት የምንመላለስ ሁሉ በመንፈስ ዝለት እንዳንጠቃ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው«በመንፈስ የምንቃጠል» /ሮሜ12÷11/ ልንሆን ይገባል።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ!